ANUAK JUSTICE COUNCIL
*Justice, Peace and Freedom*

---

# Crisis in Ethiopia: Meles Will Ultimately Fall—Are We Ready?

## ቀውስ በኢትዮጵያ፤ መለስ ይወድቃል፡ እኛ ግን ተዘጋጅተናልን?

June 21, 2008

ከአባንግ ሜቶ
ትርጉም(ሀጎስ ሀብቶምና መላኩ ፀጋዬ መኮንን)

የመለስ አገዛዝ ውድቀት እየተፋጠነ መሆኑን የሚያውቁት ኢትዮጵያውያን ብቻ ሳይሆኑ፡ የውድቀቱ ዜናና የፈጸማቸው ወንጀል ማስረጃዎች በአለም አቀፉ ማህበረሰብ ዘንድም ጭምር እየተገለጡ ነው። በመሆኑም የዚህ አፋኝ ስርአትን ጨቋኝ ባህርይ ዝም ብሎ ማለፍም አይታሰብምና የመለስ አፈናው አስቸጋሪ ነው የሚሆነው።

አንገብጋቢው ጥያቄ ይሄ ስርአት ድንገት ቢወድቅ ኢትዮጵያዊያን ሀገራችን ለገጠሟት ፈታኝ አያሌ ቀውሶች መፍትሄ አበጅተዋል ወይ የሚለው ነው። እንዳለመታደል ሆኖ፡ ዝግጁ የሆንን አይመስለኝም። ብዙ ግዜያችንን በወቀሳና እሮሮ ላይ ስናውል፡ ጥቂቱን ብቻ ነው በመፍትሄ ላይ የምናጠፋው።

ከዚህ በኋላ ወደከፋ አደጋ ሊከተን የሚችለውን ችግር ለመቅረፍ የሚያስችል አብይ ስልታዊ እቅድ ለማፍለቅ ጊዜ መፍጀትም መዘግየትም የለብንም። የገጠመን ጥፋት ምንግዜም ሊፈነዳ የሚችል ሰዓቱን የሚቆጥር የጊዜ ፈንጂ ነው። አፋጣኝ እርምጃ መውሰድ አለብን። ያለበለዚያ ለመጪው አደጋ በበቂ ያለመዘጋጀታችን ለቅርብ ጊዜና ለረዥም ጊዜ ጥቅማችን ብቻ ሳይሆን፡ ለሕልውናችንም ጭምር አስጊ ነው።

በምንወዳት አገራችን የከፋ ቀውስ እንዳይፈነዳ ካስፈለገና፡ ሲያስፈልግም በቅርብ የምናገኘው አብይ ስልት የምንቀይስበት ጊዜ አሁን ነው። ነገሮችን ለማስተካከል ከመዘግየታችን በፊት፡ ሁሉም ካገር ውስጥና ውጭ የሚገኙ አገር ወዳድ ኢትዮጵያዊያን፡ መፍትሄ በማፈላለጉ ሂደት ድርሻቸውን እንዲወጡ ጥሪ እያቀረብን፡ እነሆ ኢትዮጵያን የሚያድን የአዲሲቷ ኢትዮጵያ ትብብር ንቅናቄ/አኢትን/ የተሰኘ አመራር አካል እያቋቋምን መሆኑን እናበስራለን።

## የአዲሲቷ ኢትዮጵያ ትብብር ንቅናቄ /አኢትን/ ምንድን ነው?

ስለ የአዲሲቷ ኢትዮጵያ ትብብር ንቅናቄ ለማብራራት ያህል፤ ይህ ሌላ አዲስ ፖለቲካ ፓርቲ አይደለም። ይልቅስ ህዝባችንን አንድ ላይ ለመሰብሰብ የሚጥር አስተባባሪ ንቅናቄ ነው።ይሄ ንቅናቄ የትብብር እንቅስቃሴ የተሰኘበት ምክንያትም ዛሬ ሁላችንም በጎሳ፡ በክልላዊ ጥቅማ ጥቅም፡ በሀይማኖት፡ በጾታ፡ በእድሜና በአመለካከት የተከፋፈልን ስለሆን ነው። እንደዚህ እንደ የአዲሲቷ ኢትዮጵያ ትብብር ንቅናቄ  ያለ አንድ ወጥ የመላ ኢትዮጵያና ህብረ-ብሄራዊ ተቋም የለም።

ራሱን እንደ ህብረ-ብሄራዊና ኢትዮጵያዊ ተቋም አድርጎ የሚቆጥረው ኢህአዴግ እንኳን፡ ኢትዮጵያዊ ተቋም ሳይሆን ልክ በወርቅ እንደተለበጠ ብረት የሀሰት ድርጅት ነው።ኢህአዴግ ዘወትርም የጥቂቶችን ጥቅም በሚያራምደው ህዝባዊ ወያኔ አርነት ትግራይ የተከበበ የጥቂቶች ድርጅት ነው። ይህም ድርጅት የትግራይን ህዝብ በሙሉ ሳይሆን የራሳቸውን ጥቅም ስለሚያስጠብቁ አመራር አካሉን የሚመለከት ነው።

አዲሲቷ ኢትዮጵያ የሚለውን ቃል የተጠቀምነው፡ የምናልማት ኢትዮጵያ፡ አሁን ካለችን ወይንም ቀደም ሲል ከነበረችን ኢትዮጵያ ፈጽሞ የተለየች ስለሆነች ነው። ቀደም ሲል የነበረችው ኢትዮጵያ ምን አይነት እንደ ነበረች ሁላችንም እናውቀዋለን። እንደ ሕዝብ ለህልውናችን ምን ያህል ጠንቅ እንደነበር እናውቀዋለንና። የዚህ አገዛዝ መርዝ እያጠፋን ስለሆነ ነው ዛሬ በያቅጣጫው አያሌ ነጻ አውጪ ግንባሮች ከኛ ሊገነጠሉ የሚጥሩት። ለዚህም ነው ብዙዎቻችን ከኢትዮጵያ እንደተገለልን የሚሰማን። ለዚህም ነው ብዙዎቻችን በተለይም ከኛ መካከል የተማሩት የተሻለ እድልና ነጻነት ፍለጋ አገራቸውን ጥለው ነጻነት ወደበዛበት ምእራቡ ዓለም የምንጎርፈው።

የምንፈልጋት አዲሲቱ ኢትዮጵያ ለሁሉም እኩል የሆነች ከጎሳ ይልቅ ሰብአዊነት የሚቀድምባት፡ የህግ የበላይነት የሚሰፍንባትና ፍትህ፡ የሰው ክብር፡ ነጻነት፡ ዜጎቿ እኩል እድል የሚያገኙባት፡ ሰላምና ብልጽግና ያለአድልዎ የሚራመድባት አዲሲቷ ኢትዮጵያ እንድትሆን ነው የምንሻው። ይህም እንቅስቃሴ ኢትዮጵያን የሚያድን እንቅስቃሴ የሚሆነው በየስፍራው እየጠፋች ያለች ኢትዮጵያ ምስል ስለምንመለከት ነው። በየቦታው እየረገፉ ባሉ የወደፊቷ ኢትዮጵያ ወራሽ የሆኑ ህጻናት፡ በድርቅ፡ ረሀብና ጠኔ፡ ሕዝባችንን ለመመገብ በምናደርገው ቋሚ ልመና፡ የሰብአዊ መብት ረገጣን በሚገልጹ ተከታታይ ዜናዎች፡ በማናቸውም አይነት ፍትህዊነትና ህጋዊ ስርአት እጦት፡ አገራችንን ጥለን እንድንሄድ በሚያስገድዱን መልካም እድሎች እጦትና፡ ሚሊዮኖችን ለመርዳት በሚጥሩ ኢትዮጵያዊያን መገኖቻችንን ላይ በምንመለከተው ተስፋ ማጣት የአንድ አገርንና ሕዝብን ሞትና ጥፋት አይቀሬነት እየተመለከትን በመሆኑ ነው።

በርግጥ፡ የኢትዮጵያ ማንሰራራት አትዮጵያን ፈጽሞ ከማይተዋት ሃያሉ እግዚአብሄር እስትንፋስ ብቻ የሚወጣ የሞራል ለውጥ ይሻል። ይሁን እንጂ፡ እኛ ለእህቶቻችንና ለወንድሞቻችን የሞራል ግዴታና እግዚአብሄርን ትተነዋልን? ረስተነዋልን? እኛ ኢትዮጵያዊያን፡ በቅኝ ግዛት እንዳልተገዛን በማሰብ ራሳችንን "ኩሩ ህዝብ" አድርገን እንኮፈሳለን። ነገር ግን፡ በሚቃረኑ የጎሳና የግል ጥቅም በሚከፋፍል የጎሳ ፖለቲካ ራሳችንን እያጠፋን ነው።

በውስጣችን የሞራል ለውጥ እንዲመጣ በየዋህነት ወደ እግዚአብሄር በመጸለይና ወደ ሌሎችም በመቅረብ፡ እንዲሁም የበደሉንን ይቅርታ በመጠየቅና የጎዱንንም ይቅር በማለት፡ እውነተኛ የለውጥ ጎህ በኢትዮጵያ ሲቀድ ልንመለከት እንችላለን። እግዚአብሄር ስራችንን እንድንሰራ አያስገድደንም። ነገር ግን የሱን ሕይወት-ሰጪ መርሆች ለመከተል መምረጥ ወይም መወሰን አለብን። ያኔ ብቻ ነው የአገራችንን ሕልውና ማንሰራራት ማየት የምንጀምረው።

የትብብር ንቅናቄ ለአዲሲቷ ኢትዮጵያ ዋንኛ ተልእኮ፡ አገራችንን ነጻ ለማውጣት መንገድ ለመደልደል፡ ሁሉንም የፖለቲካና ሲቪክ ቡድኖች፡ ማለትም፡ የሀይማኖት፡ የነጻነት፡ የፖለቲካና የሲቪክ ድርጅቶች አንድ ላይ እንዲመጡ ማድረግ ነው። ሁሉንም ያላጠቃለለ ንቅናቄ ዘላቂ መፍትሄ እንደማያመጣ ይልቅስ ያለፉ ስህተቶቻችንን እንድንደግም ብቻ እንደሚያደርገን እናምናለን።

## የውድቀት ምልክቶች በፍጥነት እየቀረቡ ነው

እኛ ኢትዮጵያዊያን፡ በየቀኑ፡ ቢያንስ በከፊልም ቢሆን በመለስና የማሰኑ አጋሮቹ ምክንያት ስለአገራችን የተለያዩ ችግሮችን እንሰማለን። የችግራችን ዝርዝር ማብቂ የለውም። ከነዚህ የመለስ መንገስት በሚገርም መልኩ ከሚከዳቸው ወይም በሌሎች ላይ ከሚያሳብባቸው ችግሮቻችን መካከል የሚከተሉት ይገኙበታል።
*ድርቅና የሰብል ብልሽት፤የሚያሻቅብ የዋጋ ግሸበት፤ጠኔና የሚሊዮኖች መራብ፤የኢትዮጵያ መሬት ከጎንደርና ከጋምቤላ ለሱዳን መሰጠት፤ተቃዋሚዎች ላይ የሚደረግ ማስፈራራያና ወከባ የኢህአዴግ የቅርብ ጊዜ ምርጫ አፈና፤የብዙ ሺህ ፖለቲካ እስረኞች መታሰር፤የመገናኛ ብዙሀን መታፈን፤የተራቡትን ከመመገብ ይልቅ የወታደራዊ ወጪ ማሻቀብ፤የግብርና እድገት አለመኖር፤በአብዛናው የአገሪቱ ክፍሎች የጤና፡ የንጹህ ውሀ አገልግሎት የትምህርት እና የመሰረተ ልማት አውታሮች አለመኖር፤የግል ሀብትና የመሬት ባለቤትነት አለመኖር፤በገንዘብ ባንክ ውስጥ የተቀመጠ ወርቅ በብረት መለወጥ፤ጉበኝነትና ሙስና በከፍተኛ ባለስልጣናት ዘንድና፤ በድህነት በምትሰቃይ አገር ውስጥ በጥቂት ልሂቃን ሀብታሞችና በብዙሀኑ ድሆች መካከል ከፍተኛ የሆነ የኑሮ ልዩነት፤በኦጋዴን፡ በአፋር፡ በቤንሻንጉል-ጉምዝ ፡ በኦሮሞና በሌሎች ክልሎች የሰብአዊ መብት ሰቆቃዎች፤ከአለማቀፉ ሕብረተሰብ የማያባራ ምጽዋት፤በሁሉም የደህንነት መለኪያ ጠቋሚዎች፡ የኢትዮጵያ አንዷ መጥፎ ምሳሌ ሆኖ መካተት፤በአገሪቱ ሁሉ የተንሰራፋ ተስፋ መቁረጥ፤የመሳሰሉት ችግሮች ጠቋሚዎች ናቸው።*

እነዚህን ችግሮች ለመፍታት የአንድነት እጦት፡አንዱና መሰረታዊ ጉዳይ ነው።ከነዚህም ሁሉ በኢትዮጵያ ውስጥ ካሉ አያሌ የተወሳሰቡ ችግሮች በተጨማሪ፡ የአፍሪካው ቀንድ በጠቅላላ በውጥረትና ምን ጊዜም ሊፈነዱ በሚችሉ ግጭቶች  እየተናጠ ነው።

ለምሳሌም ያህል በኤርትራና በኢትዮጵያ መካከል፡ በኤርትራና በጂቡቲ መካከል፡ የኢህአዴግ የሶማሊያ ወረራ፡ ከሱዳን ጋር ያለው ችግር፡ በተለይም በቅርቡ  ይፋ የወጣው፡ በመለስና በአል በሺር መካከል ለሰባት አመታት ሲሰራ የቆየው ምስጢራዊ ስምምነት፡ ናቸው።

ኢትዮጵያ በምስራቅ አፍሪካ ወዳጅነትን በመፍጠርም ይሁን በአገሮች መካከል ያለን ግንኙነት በማሻከር ለኢትዮጵያዊያን ወሳኝ በሆነ መልኩ ቁልፍ ሚናን ስትጫወት ኖራለች። የተረጋጋች፡ ደህንነቷ የተጠበቀ ዴሞክራሲያዊና ነጻና የበለጸገች ኢትዮጵያ ጎረቤት አገሮችንም ይሁን ሌሎች የአፍሪካ አገሮችን በአዎንታዊ ተጽእኖ የሚያሳድረውን ያህል፡ የዚህ ተቃራኒም የአከባቢውነ እድገት አሉታዊ በሆነ መልኩ ይገልጻል።

### አንድነት ማለት በመለስ ላይ ተባብሮ መቆም ማለት ብቻ አይደለም

ነገም፡ ሌሎች ችግሮቻችን ላይ እንደርስባቸውና ብዙ የአንድነት ጥሪዎችን ልንሰማ እንችላለን። ነገር ግን ያ ማለት ምን ማለት ነው? አንደኛ እንድነት ማለት ከወሬ ባሻገር ለሌሎች በተግባር መድረስ ማለት ነው። ሁለተኛ በጋራ ጠላት ተባብሮ መነሳት ብቻውን በራሱ አገራችንን ለማቆየትና ለማደግ በቂ አይደለም። ለምሳሌ፡ መለስንና በኢትዮጵያ በሁሉም አቅጣጫ እየሰራ ያለውን ክፉ ስራ ለማውገዝ መስማማት ቀላል ነው። ዘላቂ አንድነት ማለት ግን ከዚያም በላይ ነው። ለችግሮቻችን አስቀድሞ መፍትሄ በመፈለግ፡ ለዚህም የመጪውን የአጭር ጊዜና የረጅም ጊዜ ግቦችን ያካተተ ግዙፍ ስልት በመቀየስ እንደ አገር መዋሃድ ወይንም አንድ መሆን ሂደታችንን መጀመር አለብን።

ባሁኑ ጊዜ ባብዛኞቹ በውጭ እና በአገር ውስጥ በሚገኙ የሀይማኖት፡ የፖለቲካና  የሲቪክ ተቋማት ውስጥ ከፍተኛ መለያየትን እናስተውላለን። መለስን ለመለያየታችን ምክንያት አድርገን ልንከሰው እንሞክር ይሆናል። በርግጥም መለስ የራሱን የፖለቲካ አጀንዳ ለማራመድ ለያይቶናል። ይሁን እንጂ በመጨረሻው መለስ ባወጣቸው የልዩነት ሕግጋት ለመጫወት ከወሰንን፡ እኛም የዚያ እንድንለያይ የሚያደርገን ጤናማ ያልሆነ ስርአት አካል እንሆናለን።

ብዙዎች ይሄንን ችግራችንን እየጠቆሙን ለምንድነው በልዩነት የምንቀየው? የዚህ ዋናው ችግር በኛው ውስጥ ነውና በጋራ አላፊነት እየወሰድን፡ መጪው ዘመናችንን መለወጥ ከፈለግን አስተሳሰባችንን ልንመረምር ይገባል።ፊውዳሊዝምን ሞክረነዋል። አልሰራም። ሶሻሊዝምን ሞክረነዋል። እሱም አልሰራም። ጎሰኝነትንና የሀሰት ዴሞክራሲንም እየሞከርነው ነው። እሱም እያጠፋን ነው።

እነዚህ ሁሉ ብልሹ ሞዴሎች የራሱን ሕዝብ የሚያፍን አምባገነናዊ አመራር የጠየቁ ናቸው። ምናልባትም እኛ የለመድነውና ያለን አእምሮ፡ ተሰጥኦን ችሎታንና አስተዋጽኦን የሚያበረታታ ኢትዮጵያን በጋራ የሚያንሰራራ የፖለቲካ አየር ሳይሆን፡ አጥፊ የሆነን ውድድር የሚያበረታታ መጥፎ ባህል ነው። ወደራሳችን ውስጥና ውስጣዊ ፍላጎታችን በመመልከት ሌሎችንም ከዚያ ፍላጎታችን አንጻር መገምገም አለብን። ቀጣዮ መለስን ለመሆን እርስ በርሳችን የምንዋጋ ከሆነ፡ የትም አንደርስም። ህይወታቸውን የሰዉ ኢትዮጵያዊን ሞትም በከንቱ ይሆናል።

በምትኩ እያንዳንዱ ግለሰብና ተቋም ከፍራቻ እና ከስጋት የተላቀቀ፤ ከስልጣን ጉጉነት የራቀ፤ ከጥቅምና ከራስ ውስጣዊ ፍላጎት የተገታና ከፍተኛውን የሞራል መርሕ የተከተለ እና ለሌሎች የሚሰተውን ግልጋሎት ያለምንም የቁሳቁስ ሽምገላ ለማከናወን ውስጣዊ ትግል ማድረግ ይኖርበታል።ለማሳሌ “የጉሳ ጥቅም ስለአገኘን እራሳችን ከመሪዎች ጋር እናጣብቃለን ወይንስ ለሁሉም የሚሆን የማያዳላ አመለካከት ያላቸውን መሪዎች እንደግፋልን”ለዚህ ጠቃሚ የሆነው ጉዳይ አባገነን መሪዎች እንዳይበቅሉ ከመሰረቱ እንጥራለን ወይንስ እንደመጀመሪያው  አይነት መንግስቱ ኃይለማሪያምን አባረን በሌላ አባገነን መለስ ዜናዊ እንተካለን? በመሆኑም የእኛን አስተሳሰብ በውስጥ ለመለወጥ ወይም ጨቋኝ ባል ፈቶ በሌላው ከመጀመሪያውና ከሁለተኛው የባሰ መውደቅ?

## መሠረት ያለው ስልት አሁን በግድ መጣል ይኖርበታል!

አሁኑኑ የመለስ አገዛዝ የገጠሙት ስር የሰደዱ ችግሮች ከአቅም በላይ ሁነው ከቁጥጥር ውጭ መውጣታቸው አይቀሬ ነው።ይህ ማለት ሁሉም ያበጠ ነገር ሊፈነዳ የሚችልበት ደረጃ ደርሷል።ይህንን ያበጠ ችግር ሊያፈነዳው የሚችለው ትክክለኛ ነገር ግን ምን እንደሆነ ማረጋገጥ አስቸጋሪ ነው።ነገር ግን ይህ ቁስል መፈንዳች የሚችልበት ደረጃ ላይ መድረሱን የሚያመለክቱ ጠቃሚ ምልክቶች አሉ።ሀገራችን በጣም አደገኛ ሁናቴ ውስጥ ሊከታት ወደ ሚችል ቀውስ፤ አመጽና ስቃይ እንዳትወድቅ መዘጋጀት አለብን። ከአደገኛ ችግር ሊታደግ የሚችል ሁኔታ መፈጠር ያለበት፡ ያልተዘጋጀንበት ችግር እንዲከሰት አንሻም።

ዛሬ ማንም በግልጽ ይህ መንግስት ቢወድቅ የሀገሪቱን ሰላምና ደህንነት ለማስጠበቅ ተጨባጭ ስልት ቀይሶ ያለየለም።ስህተት መፈጠሩን እናውቃለን። ግን ይህን የኢትዮጵያን ሕዝብ ሕግና ስርአት እንዲጠበቅ ፤ምግብ፤የአስቸኳይ የጤና አጠባበቅ ፤እርዳታ አስታጥና ንጹህ የመተጥ ውሃ እና መጠለያ  የሚገኝበትን ስልት በተጨባጭ ያዘጋጀ አለን?

በእርግጠኝነት የጎሳ ግጭት  እንዳይኖር፤ቂም በቀል እንዳይከሰት ከሁሉም በላይ ደግሞ አጠቃላይ ቀውስ እንዳይፈጠር ሁኔታወች ተዘጋጅተዋልን?በተለይ ደግሞ የረሀብን የኑሮ ውድነትን ፤የፍትህ ማጣትን ፤መፈናቀልን በአጠቃላይ ጭቆና ላለፉት ዘመናት የገረፈውን ሕዝብ ለመታደግ የሚያስችል ዘዴ ወይንም ስልት ቀይሰናልን?

ለመሆኑ የኢትዮጵያን ሕብረተሰብ ተቋማትን እና ሕዝቡን እንዴት በድንገተኛ አመፅ ወቅት ሊከተል ስለሚገባው መዋቅራዊ አሠራርና ስልት እና ተሳትፎውን የሚያመለክት ዘዴ አስተምረንዋል? በቅድሚያ እንዲገነዘብ አድርገናል? እነዚህ በመጀመሪያ ወቅት መደረግ የሚጋባቸው ጉዳዮች ናቸው በጣም ወሳኝ የሆኑ መሠረቶች መጣል አለባቸው እነዚህ ጥያቄዎችና ጉዳዮች በጥንቃቄ መታሰብ አለባቸው፤ መታቀድ አለባቸው በተግባርም በተከታታይ መተርጎም የኖርባቸዋል፡

በመለስ ላይ ብዙ ጫጫታና ትኩረት እኛ የምንፈልገውን ዝግጅት ሊያስከትል አይችልም ወይም ሌላ ድርጅት መመስረት ለጉዳዩ መልስ የሚሆን አይደለም ወይንም ሕዝቡ እራሱን ለመርዳት ለመሞከር ይህን ጥረት ለማስተባበር የሚሞክር የለም። ይህ ሊሆን እንደሚችል ለማዳመጥ የፈለገ የለም ሌላ ወገን እንዲሰራው ይፈልጋሉ። ይህ ወደፊት የመቅደም ተግባር ውድቀቱ ምን አልባት ከምቀኝነት ካለመስማማት፤ ከተንኮል የአርቆ ማየት አለመቻል/ እጥረት/ ወይም በመለስ አገዛዝ በሌሎች የፓለቲካ ድርጅት መፈናፈኛ ከማጣት የመነጨ ከመዋከብ ጋር የተያያዘ ነው። ምንም ይሁን ምን እንደምንም ብለን ወደፊት መገስገሳችን መቀጠል አለበት። የመዘግየት እድሉ የለንም። ያለን አማራጭ ቀጣዩን ጠንካራ ሥር ለማከናወን በሚገጥሙን መሰናክሎች ውስጥም ሆነን ስልት መቀየስ ይኖርብናል።

ለዚህም ነው አሁን የሚቀርበው ሀሳብ በጣም በፍጥነት መሠረት ያለበት ይህ የመጀመሪያ ጊዜአችን አይደለም። ኢትዮጵያን የፓለቲካ ድርጅት ያልሆነ ንቅናቄ እንዲመሰረት ጥሪ ሲደረግ ይኸው ከፓለቲካ ድርጅት ውጭ የሆነ ንቅናቄ ተግባሩን በአንድ ድርጅት ጥላ ስር በማዋቀር የወደፊቱን እድገት የሚቀይስ፣ ደህንነትንና እርቅን የሚያመቻች ሆኔታ መፍጠር ይህን ሀስብ የቅንጅት መሪዎች እስር ቤት በነበሩበት ወቅት ከተፈቱም በኃላ ተከፋፍለው የብዙ ኢትዮጵያውያን ቅስም ሳይሰብሩ ይኸውኑ ጥሪ አቅርበናል።

እንደገናም በህዳር 17/2007 በዋሽንግተን ዲሲ ተመሳሳይ ንቅናቄ እንዲኖር ጥሪ አቅርብን ነበር። ኢትዮጵያውያን ከተለያዩ ክልሎች አካባቢዎችና የተለያዩ የማህበረሰብ ስብጥሮችና የኀሳ ቡድኖች በጋበዝንበት የግንቦት 15 –18 የአለማቀፍ ንቅናቄ ዘመቻ ወቅት ተመሳሳይ ጥሪ አድርገናል። እነዚህ ሁሉ ጥሪዎች የሚያመለክቱት ለምን በአንድ ላይ ለመነሳት እንዳቃተን እና መለስ ዜናዊን ይችን ሀገር እንዲያጠፉና የያዘውን እቅድ ልብ እንዲመታ እድል እንሰጠዋለን። በዚህም ምክንያት ለወደፊቱ ለሚመሰረት ለአዲሲቱ ኢትዮጵያ ትብብትር ንቅናቄ እራሳችንን ማዘጋጀት የኖርብናል።

በርካታ ችሎታ ያለቸው ኢትዮጵያውያን በመሰበሰብ ላይ ናቸው ከእነዚህ በጣም የተከበሩ መሪዎች መካከል ዶ/ር ጉልቶ ኤላ ከኢትዮጵያ ትብብር ፎረም አንዱ አለማቀፍ ግስጋሴ ኮሚቴ ጋር የተቀላቀሉበትን ምክንያት ሲያስረዱ ይህንን የሀገራችን የኢትዮጵያን ሰቆቃና ሰቃይ ብሎም መከራ እየሰሙ መቀመጥ ሕሊናቸው ሊሸከመው አለመቻሉን ገልጠዋል።

በርካታ ታላላቅ ሰዎች አስተዋይ እና እራሳቸውን ለኢትዮጵያ ጉዳይ የቆሙ እና ከተለያዩ የብሄረሰብ የሃይማኖት እና አካባቢ የተሰባሰቡ ሊኖሩ እነዚህን ሁሉ በስም ዘርዝሬ ለወግለጽ እጀገራለሁ በመሆኑም እንደ ፐ/ሮ ማም ሙጨና ፐ/ሮ አለማየሁ ገብረማርያም የመሳሰሉትን ልጥቀስ እነዚህን ግለሰቦችና ሌሎችንም በእውቀታቸው /በጥበባቸው እና ሀገራቸውን በመወደድ በጣም አደንቃቸዋለሁ። ከእኛ ጋር የተቀላቀሉት ቀባዮ መለስ ለመሆን አይደለም ነገር ግን ኢትዮጵያ ከተጋረጠባት መዥገር ነፃ ለማውጣት ነው።

## አስቸኳይ ለሆነ ገጠመኝ አጣዳፊ የአጭር ጊዜ እቅድ

በኢትዮጵያ ውስጥ አጣዳፊ ሁኔታ ቢፈጠር መልስ ለመስጠት እንዲቻል የተወሰኑ ግለሰቦች ለአጭር ጊዜ እቅድ እንደዘጋጁ ማድረግ እጅግ በጣም አስፈላጊ ነው።በአሁኑ ወቅት በኢትዮጵያ የአለማቀፍ ግስጋሴ ለነፃነት ለሰብአዊ መብትና ለፍትህ አዘጋጅ ኮሚቴ አማካኝነት የአስቸኳይ ጉዳይ መልስ ሰጭ ቅድመ ዝግጅት ተጀምራል። ይህን የሩቅ ትንበያን የሚሰራ ጠንካራ እና ለጉዳዬ እራሳቸውን ያዘጋጁ ወሳኝ ሰዎች በቡድን ደረጃ ተውጣጥተው አንድ አመራር የሚሰጥ ቡድን ከተለያዪ ክፍሎች የተውጣጣ ይህንኑ ተግባር የሚያከናውኑ በመደሪጀት ላይ ነው። ይህን ግልፅ ለማድረግ የምንሻው ሌላ የፓለቲካ ፓርቲ መመስረታችን አለመሆኑ እንዲታወቅ ሆኖም ግን በጣም እንስቸኳይ የሆነውን ጉዳይ እራሳቸውን ያዘጋጁ ጥቂት ግለሰቦች እንኳ ቢሆኑ መሠረታዊን ስራ በመስራት ሌሎች እንዲመጡ የማድረግ ተግበር ሊያኮናውኑ የሚችሉ መሆኑ ነው።

የሁሉም ፓለቲካ ፓርቲዎች፤የማህበረሰብ ድርጅቶች የሀይማኖት ቡድኖች እንዲሁም ሌሎችን ቡድኖች በኢትዮጵያ ውስጥ ፍትህን፤ ነፃነትንና ብልፅግናን ለማምጣት የሚያደርጉትን ጥረት እናደንቃለን። እኛ ከማናቸውም ጋር ውድድር ውስጥ አልገባንም ነገር ግን ከተለያዪ ቡድኖች ጋር ለሀገራችን የሚሠሩትንና በተለይም ለሁላችን መኖር ከሚሠሩ ጋር አብረን ለመስራት ዝግጁ ነን። ምን አልባት የተለዬ የአሠራር ስልት ልንመሳሰል አንችል ይሆናል። ተስፋ እንደምናደርገው ወደፊት ስራችን ስንቀጥል ይቀላቀሉን ይሆናል። እንደዚሁም መለስ ለተቃዋሚ ቡድኖች ምን ያህል አስቸጋሪ ሁኔታ እንደፈጠረባቸውም ይገባናል። ተስፋችንም እርስ በእርስ እንረዳዳ ይሆናል የሚል ነው።

በሌላ አባባል እኛ እየጠበቅን ያለነው ይህንን ነው እናንተስ? በጋራ ሀገራችን ነፃ እናወጣለን። አላማችን ቀጣዩ መለስ መሆን አይደለም። በአንፃሩ እውነተኛ ዴሞድራሲ በኢትዮጵያ ውስጥ መሠረት እንዲጥል ለኢትዮጵያ ጤናማ አካባቢ እንዲፈጠር በተግባርም ዜጎችም ተሳታፊ እንዲሆኑ ማድረግ ነው። ይህ ቡድን አሁን በአደጋ ላይ/በመፊራረስ/ ላይ ያለች ኢትዮጵያን መታደግ አለበት የተለያዩ ዓላማያዎችን ድጋፍና እርዳታም ይሻል። ነገር ግን ስራው ያለምንም መዘግየት መጀመር አለበት። በሙሉ እምነት ባለሙያዎች ይመጣሉ ብለን እናምናለን፤ አሁን አስችኳይ ጥረታችን በፍጥነት የመለስ መንግሥት ሲወድቅ በጣም መሠረታዊ የሆኑ የአስቸኳይ ጊዜ የአጭር ወቅት እቅድ ማዘጋጀት ነው ይኸውም፣

1. ኢትዮጵያ ውስጥ ሕግና ስርዓት ተጠብቆ ሕዝቡ ሰላምና ደህንነት እንዲጠበቅ እንዴት ማረጋገጥ እንደሚቻልና ይህንንም ሁሉም ሕዝብ እንዲያውቅ ማስቻል፣

2. ዘጠኝ ሚሊዮን በረሃብና የተመጣጠነ ምግብ እጦት የሚሰቃዩትን እንዴት መርዳትና መመገብ ይቻላል? የብዙዎቹ ሕይወት በርሃብ ምክንያት አጠያያቂ ድረጃ ላይ ነው ያለው፤
3. የግብርናውን ሀብት በሃገሪቱ ውስጥ በአግባቡ ለማሳደግ መወሰድ የሚገባውን ተግባር በተመለከተ፤
4. በሀገሪቱ በፍጥነት እያደገ የመጣውን የኑሮ ውድነትና የምግብ መወደድን እንዴት ማስወገድ እንዲሚቻል፤
5. ሰላምና መረጋጋት በሀገሪቱ እንዴኖር አንዱ ከሌላው መለያይቱና ፀበኛ በሆኑ ቡድኖች መካከል እንዴት አንድነት መፍጠር እንደሚቻል፤
6. ለፍትህ ለእርቀ ሰላምና ለዴሞክራሲ እንዴት ቅድመ መሠረት ሊጥል የሚችል ተግባር ማከናወን እንደሚቻል፤

## ኢትዮጵያ ውስጥ የመገናኛ አፈናው በግድ መሰበር አለበት።

ኢትዮጵያ ውስጥ ሕዝቡ መረጃ የሚለዋወጥበት ማገናኛ ዘዴ መፈለግ አለበት። አብዛኛዎቹ የመረጃ መለዋዋጫ መስመሮች በሚገባ በኢህአዴግ ተዘግተዋል።ነገር ግን በጣም ዘዴና የፈጠራ ችሎታ ያላቸው ኢትዮጵያውያን ይህንን መሥናክል ቆርጠው ሕዝቡ በአግባቡ መረጃ እንዲለዋወጥ ማድረግ መቻል አለበት። በዚህ ረገድ የገንዘብ አቅም መጎልበት አለበት። ይህንኑ የግንኙነት መስመር ለመዘርጋትና በተግባር ለማዋል የሚያስፈልገውን ወጭ መሸፈን የሚችሉ በርካታ ኢትዮጵያውያን የገንዘብ አቅም ያላቸው አሉ። ጊዜው አጣዳፊ ነው። ከእነዚህ ሰዎች እርዳታ እንሻለን፡ ኢትዮጵያ ውስጥ ያለው ነገር ቢበላሽ/ቢፈነዳ ሳንዘጋጅ በመሀል መያዝ የለብንም።

## እራሳቸውን ለዚህ ተግባር ያዘጋጁ ሙያተኖች ይፈለጋሉ!!

ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያን ያልሆኑ የኢትዮጵያ ወዳጆች ባለሙያዎች ማለትም በግብርና በኢኮኖሚ ልማት፤ በግል ሥራ የሚሰማሩ፤ በመሬት ይዞታ፤ በጋዜጠኝነት፤ በአስተዳደር፤ የወንጀል ተከታታዮችና የሕግ በለሙያዎች፤ በትምህርት ዘርፍ፤ በቤተሰብና በማህበራዊ ችግሮች፤ በጤና በሕግ፤ በዳኝነት እና በምግብ አሰረጫጨት፤ የሃይማኖት መሪዎች፤ የሰብአዊ መብት ተከራካሪዎች እና አርቀ አስተዋይ አሳቢዎች እንደዚሁም የሰብአዊ እርዳታ ሠራተኖች ከሲቪል በማህበረሰብ ጎን ለጎን ያስፈልጋሉ። እነዚህ ሁሉ ኢትዮጵያን እንደገና በመገንባት በማስታረቅና በማስማማት የኢትዮጵያን ሕብረተሰብና ተቋማትን እንደገና በማደረጀት የሚያገለግሉ ሙያተኖች ያስፈልጋሉ።

በአለማቀፉ ማህበረሰብ የኢትዮጵያን ጥቅም ለማሳወቅ የተባደነ ስራ ማከናወን ያስፈልጋል። በተለያዩ አጋጣሚዎች ከመንግስታት መሪዎችና መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች የፓሊሲ አውጭዎችና አመራር ሰጭዎች የሚሰነዘረው አስተያየት የኢትዮጵያን ሕዝብ ፍላጉት በአለማቀፍ ሕብረተሰብ ተሰሚነት  እንዲኖር ከተፈለገ ኢትዮጵያውያን አንድ ሆነው በአንድነት ድምፃቸውን ማስማት ይኖርባቸዋል ነው የሚሉን፡ ይህ የአመራር ቡድንም እንደዚህ አይነቱን ጉዳይ በአንድ ላይ ሆኖ ግፊት ማድረግ አለበት። የአመራር ቡድኑ በባለቤትነት ስሜት ግፊቱን ማበርታት ይኖርበታል ለወደፊቱ ተጨባጭ የሆነ አንድ ነገር ሕገዊነትን የሚያስከትል መከናወን አለበት። ኢትዮጵያን የሚያጠነክርና የሚያረጋጋ በደንብ የተቀነባበረ ስልት መቀየስ ይኖርበታል። ለውጥ ምንም ከፍተኛ ሀለፊነትን የሚጠይቅ ጉዳይ ቢሆንም ለአፋጣኝና ለሩቅ የሚያገለግል እቅድ መንደፍና ሕዝብ የራሱ ጉዳይ እንዲኖረው ማድረግ አግባብ ነው።

## እርስ በእርስ ከመወዳደር መፍትሄ በመፍለጉ ላይ ማተኮር ይኖርብናል!!

መፍትሄ ከመፈለግ ይልቅ እርስ በእርስ በንትርክ ውስጥ ስንገባ የሚፈጠረውን ጉዳይ አስቡት፤ ገምቱ እስኪ ከጭንቅላታቸው ላይ ያለ ቆብ በእሳት እየተያያዘ ያሉ ልጆች በአሻጉሊት የእኔ ነው የእኔ ነው እያሉ እንደሚጣሉት  አይነት ማለት ነው። አደጋ ላይ ናቸው ነገር ግን ሁኔታውን ለመቀበል አልተዘጋጁም በሕይወታቸውና በንብረታቸው ላይ የተደቀነውን አደጋ አላጤኑትም። ልጆቹ ሕይወታቸውንም ጨምሮ ሁሉን ነገር ከማጣት አንድ ላይ ሆነው እሳቱን ማጥፋት አለባቸው ይህን ለማድረግ ደግሞ  በአሻንጉሊት መጣለታቸውን ማቆም አለባቸው።

እኛ ኢትዮጵያውያን አሁን ለስልጣን የምናደርገው ጠብ መቆም አለበት። ይህ ካልሆነ ሁሉንም ነገር ልናጣ አንደምንችል ማውቅ ይኖርብናል፤ ማስብ ይጠበቅብናል ለወደፊቱ ማቀድ ይገባናል።

ይዚህ ቡድን ዋና የትኩረት አቅጣጫም ይህ ይሆናል። ሊገጥሙን ለሚችሉ መሠረታዊ ችግሮች መፍትሄ ለመስጠት እርምጃ ለመወሰድ ተዘጋጅተናል። ምክንያቱም ይህን ጉዳይ ማቆየት የኢትዮጵያንና ሕዝቡን  ለሚወዱት ሁሉ ሞት ፍርድን መጠበቅ አይነት ነው። የኢትዮጵያ ችግር በጣም ውስብስብ ነው በመወደቅ ላይ ያለችውን ሀገራችን ለመታደግ መፍትሄው በኢትዮጵያውያን እጅ ነው ጊዜውም አሁን ነው።

የኢትዮጵያ የመጭው ዘመን መሪ ለመሆን አጀንዳ/መርሃ ግብር / የለንም ይህን የምናደርገው ሀገሪቱን ነፃ ለማውጣት ነው። ይህን ካልን ሁሉንም በአንድ ላይ ለማምጣት በእኛ በኩል ፍላጎታቱና ተስፋው አለን፤ በውጭ ሀገር የሚገኙት በመካከላቸው እየተደራጁ እንዲወያዩ በማድረግ እንጀምራለን። በጋራ አጀንዳ ከተማመኑ በኃላ በሀገረ ቤት ካሉት ጋር ለማገናኘትና ሁሉም ተቃዋሚ በአንድ ጠረጴዛ ዙሪያ በማቀራረብና መንግስትን ደግሞ በሌላ ጠረጴዛ አስቀምጦ በደቡብ አፍሪካ እንደተደረገው በኢትዮጵያም ያለውን ችግር መፍትሄ መፈለግ ነው።

በእርገጥ የፓለቲካ ድርጅቶች አጀንዳቸውን ወደ ጎን አስቀምጠው ሀገሪቱ ነፃ እንድትወጣ በማድረጉ ሂደት ለመፍትሄ ከተዘጋጁ ይህ ተግባር ይፈፀማል ብለን እናምናለን።

እኛ እንደ አግባቢና አገናኝ ሆነን ለመስራት ነው የምንፈልገው። በነፃነት በፍትህ የሁሉም ኢትዮጵያዊ ክብር እስከተጠበቅ ድረስ ማንንም ቡድን ማግለልና ማዳላት የለም። ሌሎች እስከሚሡሩት መጠበት ከአሁን በኃላ የለም። ይህን ጎዳና መከተል አለብን። እግዚአቡሄር ከፈቀደልን በከፍተኞ ጥንቃቄና ብልሃት እንቀጥላለን። አንድዬ ስራችንን እንዲያሳካልን እንፀልያለን።

ግለሰቦችም ሆኑ በድርጅት ደረጃ ለመሳተፍ ለምትፈልጉ ሁሉ በደስታ ለቀበልና ከእናንተ ለመስማት በጉጉት ላይ ነን። በመከከላችን እንቅፋት የሚሆነውን ነገር ሁሉ አስወግደን አንድ እንሁን እግዚአብሄር ኃይሉን ይስጠን መንገዳችን ይምራ!

ትንቢተ ኢርሚያስ ም, 29, ቁጥር 11-14 “ለእናንት የምስባትን እኔ አውቃለሁ ፍፃሜና ተስፋ እስጣችሁ ዘንድ የሰላም ሀስብ ነው እንጂ የከፋ ነገር አይደለም እናንት ትጠሩኛላችሁ ሂዳችሁም ወደ እኔ ትፀልያላችሁ እኔም እስማችኃለሁ እናንት ትሹኛላችሁ በፍፁም ልባችሁም ካሻችሁኝ ታገኙኛላችሁ ከእናንተም ዘንድ እገኛሉሁ” ይላል

ለሌሎች መረጃዎች አቶ ኦባንግ ሞቶን በዚህ አሜል አድራሻ ይጠይቁ።
***[Obang@anuakjustice.org](mailto:Obang@anuakjustice.org)***